አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

ገለታ ይድረሰው፡ ሩሁን ላነገሰው፤

ከተውሂድ ጀረት ላይ፡ ለኛ እንዳፈሰሰው፤

ከውኑን ሰርቶት ላንቱ፡ በልፍኙ ደገሰው፤

ኧሃ! አልፎ አዝልቆት፡ ለኛ አወረሰው፤

በራህመቱ መርጊያ፡ ከውናቱ የረጋው፤

ከነቢ ስፍራነው የራህመት መፍለቂያው፤

ለርሶ የሾማቸው ሰጥቷቸው ካደጋው ፤

ለሥሙ ሸክረው : ተገኙ ከሊቃው፤

አሃ! ጨለማውን ራስ፡ ሸበት እስኪያነጋው፤

ጉልበታቸው አልቆ፡ መሬት እስኪያድኸው፤

ፈርጣማው ክንዳቸው፡ ከአለት የጠናው፤

የእርጅና ጉጠት፡ እስኪሸበሸበው፤

የኡምራቸውን ጠጅ፡ ለሀዱ እስኪጠጣው፤

በሁቡህ አልቅሰው፡ እንባቸውን ጨርሰው፤

እናቱን እንዳጣ፡ ህፃን ተንፈቅፍቀው፤

ሐዘን ፊታቸውን፡ ዳምኖ እስኪያጠቁረው፤

በትካዜ መርከብ፡ እንዳለ ተጭነው፤

ቀናት በነሱ ላይ፡ ያልፋሉ ተቆጥረው

አሃ! ደግሞ ሲያሥደሳቸው፡ ደርሶ ጀማሉሁ፤

የፊታቸው ጀንበር፡ ግርዶውን ጥሳው፤

ሳቃቸው ይነጋል፡ ሸሽቶ ጨለማው፤

ደምቃ ትወጣለች፡ ሐዘንን ገፋው፤

በየደረሱበት፡ ነቢ እሚከርሩ፤

ጠልፎ ይዟቸው ነው፡ የፈይዷቸው ዳሩ፤

በነቢ መንገድ ነው፡ ሲያደምጡም ሲያወሩ፤

ዚክረዎን ሲያጎርፉ፡ ላንዴም ሳያበሩ፤

ከነርሱ እስቲያልቅ፡ ተንጠፍጥፎ ዑምሩ፤

በቀብሩ አዳራሽ፡ ድግስ ተደግሶ፤

ዘልቆ እስቲጠራቸው፡ መለከል ሞት ደርሶ፤

በሩሃቸው ሜዳ ድንኳን ተቀልሶ፤

ነቢን እየጠሩ አለቁ በለቅሶ::

አለቁ በለቅሶ::

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ(3)

ሆ፤ በውበቱ ድርማ፡ ላይ፡ ውስጡ ታንጦ፤

ሁሉንም በለጠው መጨረሻ መጥቶ፤

ሸርክን ገለባብጦ በተውሂድ አንጦ፤

ዓበራው ዓለሙን በኑር እየቀባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

መፈጋፈግ'ንጂ ማን ሊችለው ነእጁን፤

እንቅጩን ለማስፈር የርሱን ዛት ሲፈቱን፤

ማን በነገረልኝ ሆዴ መባባቱን፤

እጅ.ማሰጠቱን፡ የሙስጦፋ ሐይባ፡

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

ገና ፊት'ም ሆኖ፡ ካናተሆ ማፀን፤

ጫሊዩ ቢታጩ፡ መድሁን ለማጠንጠን፤

ስንቱን ሙት አነቁት፡ ሶለዋት በማጠን፤

ለኛውም ይሰጠን፡ የነርሱ ሙሃባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

የርሱ ሥም አይደል ወይ? ሲዲቅን ያላቀው፤

ዑመሩል ፋሩቅን፡ በከሸፍ ያደመቀው፤

ዑስማንን የሃያዕ፡ ዝናር ያስታጠቀው፤

አሊን ያሳደገው፡ ሂዳያ እያጠባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

የቡሰይሪን ፈሊጅ፡ ሥርሩን ያፈለሰው፤

የቡራኢን ሀዘን፡ ጠራርጎ ያበሰው፤

የዘቡራ ልጂን፡ ልሳን ያቀመሰው፤

አንዩን፡ ዳንዩን፡ መቃም ያደረሰው፤

አብደሪይዩን በኢልም፡ ጅህልን ያስገረፈው፤

ሸይኽ አሊ ጎንደርን ሞት ያስቀሰቀሰው፤

ስንቱን አነገሰው፡ ከኸልዋ እያስገባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

በልቼ እየጠጣሁ፡ ይርብ ይጠማኛል

መድሀኒት ወስጀም፡ አጥብቆ ያመኛል

መከዳ ታቅፌ፡ እንቅልፍ ይርቀኛል

መነመነ ጅስሜ፡ ናፍቆት እየሰባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

ጀሊሉ የርሱን ሥም፡ በክብር ሲያኖጋው፤

በተጠራ ቁጥር፡ ባንድነት ያስጠራው፤

እሱ-ነው አማላጅ፡ እርሱ ነው ባላልጋው፤

ከውኑን ያረጋጋው መስመር እያስገባ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፉ ሶላት፡ የፍቅርሆ ንጋት

የኔ ጌታ፡ በላዩ ላይ ዘልቆ፤

አልፉ ሶላት፡ የሠራ አካላቱ

የኔ ጌታ፡ ያልቃል እንባ ፈልቆ፤

አልፉ ሶላት፡ ከውስጥ እየገባ
የኔ ጌታ፡ ትንፋሹን ሰንጥቆ፤

አልፉ ሶላት፡ ያስወተውተዋል
የኔ ጌታ፡ ያን ጨረቃ ናፍቆ፤

የኔ ነቢ፡ ይወድቃል ተንጋሎ
ወለላዬ፡ አረፋውን ደፍቆ፤

ጌታዬዋ! ነብሱን ያስተዋል
የኔ ጌታ፡ ልቡ ተሰንጥቆ፤

አልፉ ሶላት፡ ይዞ እያነፈለው
አልፉ ሶላት፡ ውስጡን አሟሙቆ፤

የኔ ጌታ፡ ትድረት የተባለ
አልፉ ሶላት፡ ይተወዋል ልቆ፤

አልፉ ሶላቱ፡ ጀንበር ከመዲና
የኔ ጌታ፡ እየታየው ዘልቆ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ
አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፉ ሶላት፡ አንቺ የኸይር ንፋስ
የኔ ጌታ፡ ገልጠሽ የልቤን፤

አልፉ ሶላት፡ ብለሽ ንገሪልኝ
ወለላዬ፡ ለዛ መኮነን፤

እህህ!! ዛሬስ አዳረሰው
አልፉ ሶላት፡ የሰራ አካሉን፤

የኔ ጌታ፡ ጉበቱ ነደደ
አልፉ ሶላት፡ አፈላው ደሙን፤

የኔ ጌታ፡ ሥጋውን ጨርሶ
አልፉ ሶላት፡ አወራው ጅስሙን፤

የኔ ጌታ፡ አበደ ጨርሶ
የኔ ጌታ፡ ወሰደው ልቡን፤

አልፉ ሶላት፡ አካላቱ አለቀ
የኔ ጌታ፡ ተፍቆ እንዳ'ንጀት፤

የኔ ጌታ፡ ሥጋውን አፍግቶ
የኔ ጌታ፡ ይሄዳል ባጥንት፤

የኔ ነቢ፡ ጉበቱ ሁሉ ሳስቶ
አልፉ ሶላት እንደ ወረቀት፤

የኔ ጌታ ሲቆም ደህን መሳይ
አልፉ ሶላት ልብስ ሸፍኖት፤

የኔ ጌታ ነው'ንጂ እስከቀኑ
የኔ ጌታ ነው'ንጂ እስከቀኑ
አልፉ ሶላት አይተርፍም ተ'ሞት፤

‹ወለላዬ› አድርጉልኝ እዝነት
አልፉ ሶላት፡ የብርሃን እልፍኝ፤

የኔ ጌታ፡ አኳኋኔን ሁላ
የኔ ጌታ፡ እንድትነግርልኝ፤

‹አልፉ ሶላት› አካላቴ አለቀ
አልፉ ሶላት፡ ጉልበቴም ከዳኝ፤

የኔ ጌታ፡ አጥንቴም አለቀ
የኔ ጌታ፡ ደሜ አቃጠለኝ፤

አልፉ ሶላት፡ ቀኑም ተራዘመ
ጌታዬዋ፡ እኔንም ጎዳኝ።
ሰይዲ ያረሱለሏህ
አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

ጌታዬዋ፡ ምን መክሳት፡ ብቻ ነው
አልፉ ሶላት፡ ከቶም፡ አለቅን እንጂ፤

የኔ ጌታ፡ አጣልፎት ማበሉ
አልፋ ሶላት፡ የናፍቆቱ መውጂ፤

የኔ ጌታ፡ እዋኛለሁ ብሎ
አልፋ ሶላት፡ ታንኳ ሳያበጅ፤

የኔ ጌታ፡ ተሻግሮ ሊጠለም
የኔ ጌታ፡ ያንን ባለ አዋጅ፤

የኔ ጌታ፡ የመዲናን ጀንበር
አልፉ ሶላት፡ ያ'ሸራፎቹን በርጅ፤

የኔ ጌታ፡ ጠጣውና ሁሉም
የኔ ጌታ፡ የፍቅርሁን ጠጅ፤

ጌታዬ! የቀመሰ ኖረ
አልፉ ሶላት፡ ጥሙን ሲያደራጅ

የኔ ጌታ፡ የተቀረው ሞተ
አልፉ ሶላት፡ አሸሮ በግዳጅ

የኔ ጌታ፡ እንዳቅሙ አርጉለት
የኔ ጌታ፡ መጠጫውን እንጅ

‹ጌታዬዋ!› በገንቦም በጋን
አልፉ ሶላት፡ በብርጭቆም በእጅ፤

አልፉ ሶላት፡ ዘግኖ ነው ያላቅሙ
አልፉ ሶላት፡ ፎጫ ያለው እንደ‘ልጂ፤

አልፉ ሶላት፡ ዘግኖ ነው ያላቅሙ
የኔ ጌታ፡ ፎጫ ነው እንደ‘ልጂ፤

አልፉ ሶላት፡ ዘግኖ ነው ያላቅሙ
የኔ ጌታ፡ ፎጫ ነው እንደ‘ልጂ::

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

ጌታዬዋ፡ የኑሩ ቡቃያ
አልፉ-ሶላት፡ የበረካዉ ቀንዲል
የኔ-ጌታ፡ የሙሂባች ወረት
የኔ-ጌታ፡ የመኽሉቃቱ ሹም።

ጌታዬ፡ የዓለሙ ጀንበር
አልፉ-ሶላት፡ የነጃሺ ግጣም።

የኔ-ጌታ፡ ከዉኑን ያዳከረዉ
የኔ-ጌታ፡ ትዝታዎት ኢምም።

የኔ-ጌታ፡ የሐብቴ ክብረቴ
የኔ-ጌታ፡ የሩህ ደጇ ሰላም።

አልፉ-ሶላት፡ የከዉኑ መሳሪያ
የኔ-ጌታ፡ የዓለሙ ዋልታ።

ጌታዬ-ዋ፡ የጀሊል ፊት ወደድ
አልፉ-ሶላት የፍጥረቱ አይነታ።

የኔ-ጌታ፡ የኸይሩ አዳራሽ
የኔ-ጌታ፡ የቁርአኑ ቦታ።

የኔ-ጌታ፡ የብይኑ ደጃፍ
የኔ-ጌታ፡ የሐቁ ኮረብታ፤

አልፉ-ሶላት፡ ዓዲሉ መኮንን
አልፉ-ሶላት፡ ዓዲሉ መኮንን
አልፉ-ሰላት፡ የሞላዉ እርካታ

‹‹ወለላዬ፡ ምን ጨለማ ሆኖ››
አልፉ-ሶላት፡ ቢያልፍም ከድንበር

የኔ-ጌታ፡ ከሩቁ ዛት'ሆ
አልፉ-ሶላት፡ ይታይ ነበር

የኔ-ጌታ፡ ወለል አርጎ አብርቶ
የኔ-ጌታ፡ በፊትሆ ኑር

አልፉ-ሶላት፡ ከኂላም ከፊትም
የኔ-ጌታ፡ ሚዳም ቢሆን ዱር::

ሰይዲ ያረሱለሏህ
አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

የኔ-ጌታ፡ የለም ቀና ብሎ
አልፋ-ሶላት፡ የሚያየዉ ግንባሩን

አልፋ-ሶላት፡ አንድ እንኳ አይገኝም
የኔ-ጌታ፡ ያገኝዉ ሚስጥሩን፤

ጌታዬ፡ ሁሉም ተመለሰ
አልፋ-ሰላት፡ እያጣ ሚስጥሩን፤

የኔ-ጌታ፡ አይን ያጭበረብራል
አልፋ-ሶላት፡ ሰንጥቆ ጫሬዉን፤

የኔ-ጌታ፡ የድንበሩን መለስ
አልፋ-ሰላት፡ እንኳን ሊያገኙት፤

የኔ-ጌታ፡ ባህሩ እያሰመጠዉ
አልፋ-ሶላት፡ አልቋል ብዙ ፍጥረት፤

የኔ-ጌታ፡ ወለል ብሎ እያየ
የኔ-ጌታ፡ የፊትሆ ንጋት፤

አልፋ-ሶላት፡ ይበልጥ ይቃጠላል
የኔ-ጌታ፡ ዉስጡ ታክሎበት፤

የኔ-ጌታ፡ እያንሰፈሰፈ
የኔ-ጌታ፡ እያንሰፈሰፈ
አልፋ-ሶላት፡ አካሎን ጠብሶት፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ
አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

አህዛዜ!! ምን ያለ መተት ነዉ
አልፋ ሶላት፤ ሽታዉ የሚያሳብድ፤
የኔ ጌታ፤ ቢጠጡት አይሰለች
የኔ ጌታ፤ ጥማት አያስወግድ፤
ጌታዬዋ፤ ከሆድ የማይጠፋዉ
አልፋ ሶላት፤ ግለቱ የማይበርድ፤
አልፋ ሶላት፤ አካላት እንደ ጧፍ
አልፋ ሶላት፤ አያይዞ ሚያነድ፤
ጌታዬዋ ፤ አካላት እንደ ጧፍ
አልፋ ሶላት፤ አያይዞ እሚያነድ፤

የኔ ጌታ፡ ላይ በላይ ግለቱ

አልፉ ሶላት፤ ዘውትር እሚጀደድ፤

የኔ ጌታ፤ የሸተተዉ እንኳን

የኔ ጌታ፤ ለነዛ ሲወርድ፤

የኔ ጌታ፤ ቁጭ ብሎ ድንገት

የኔ ጌታ፡ እሙሂቦች ዘንድ፤

የኔ ጌታ፡ ይጣበቅበታል

አልፉ ሶላት፡ ያመጣል መዉደድ፤

የኔ ጌታ፡ ወንጀሉ ታብሳ

አልፉ ሶላት፡ ይሆናል ሰኢዲ፤

የኔ ጌታ፡ ለነብሱም ተጠቅሞ

አልፉ ሶላት፡ ሰዉን እሚፈይድ፤

የኔ ጌታ፡ ምን ያለ ደግ ነዉ

አልፉ ሶላት፤ ሙሂባች ጋር ኑሮ፤

ጌታዬዋ፤ የቀልብን ድርቅና

አልፉ ሶላት፤ ያርቃል አባሮ፤

የኔ ጌታ፤ ትድረት ያሳምራል

የኔ ጌታ፤ ላይ በላይ ጨምሮ፤

ወለላዬ፤ ዉበት እያከለ

አልፉ ሶላት፤ ዉበት እያከለ

አልፉ ሶላት፤ መብራዉን ሰባብሮ፤

የኔ ጌታ፤ ኢምንን ያመርታል

አልፉ ሶላት፤ ነብስያይቱን ሰብሮ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ አልፉ ሶላት ወሰላም ዓላ፤ ሰይዲ ያረሱለሏህ

ጌታዬዋ፤ እንዴት'ነሁ ሙስጠፉ፤

አልፉ ሶላት፤ እንዴት ነሁ የኔ ሹም፤

አልፉ ሶላት፤ እንዴት ነሁ የኔ ሹም፤

አልፉ ሶላት፤ እንዴት ነሁ የኔ ሹም፤

የኔ ጌታ፤ ሰላሙን ሙአበድ

የኔ ጌታ፤ ይዉረድ በላዬት፤

አልፉ ሶላት፤ በቤተሰቦቹም

የኔ ጌታ፤ በአስሃቦቹት፤

የኔ ጌታ፡ ቁጥር የማያዉቀዉ

የኔ ጌታ፡ ብዙ ሶላዋት፤

የኔ ጌታ፡ የሐፊን ቀለም

ጌታዬዋ፡ ባንጠፈጠፉት፤

ጌታዬዋ፡ ቃላት በመፈለግ

አልፉ ሶላት፡ አቅልን ባለፉት፤

የኔ ጌታ፡ በስልምና ጮራ

የኔ ጌታ፡ በዲኑ መብራት፤

አልፋ ሶላት፡ ተወርዋሪ ኮከዕባ

የኔ ጌታ፡ ቀድመዉ በጣሉት፤

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤

አልፋ ሶላት ወሰላም ዓላ፤

ሰይዲ ያረሱለሏህ

Tellegram @MuhammedNessim
YouTube Nessim Almuhaba
Facebook: Nessim Almuhaba